# <u>የሚሊየኔሙ ችቦ ካሁኑ ይያያዝ!</u>

ዘነበ በቀለ

ያለመታደል ሆኖ ባለፉት ዘመናት ሁሉ ኢትዮጵያ ለሚወዷትና ለሚያፈቅሯት ምቹ ሆና አታውቅም። ስለዚህም ጉዳይ በትውልድ መሃል የሚገኙ ዜጎቿ ተመሳሳይ ግንዛቤ ነበራቸው። ብዙ ጊዜ እንደሚሰማው ይህ ሁኔታ 'ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ - የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" ተብሎም የግጥም ስንኝ ተችሮታል። ለምንድነው ኢትዮጵያ የወዳጆቿና የልጆቿ ከለላ መሆን ያልበቃችው? ለምንድንስ ነው "ሞቱና ድህነቱ" ያፍቃሪዎቿ ቀሪ ውርስ ሆኖ የዘለቀው? ይኸ አይነቱ እንቆቅልሽ መልስ ያጣ ነው። ግለኞች ብዙሃኑን እስከ ስልጣናቸው መዳረሻ ከነሽካፋቸው አዝለው እንዲያጓጉዟቸው ሲለማመጡ ይቆዩና ጉዳያቸው ሲፈፀም ሀይላቸውን የሚፈትኑባቸው ክብራቸውን የሚነጥቋቸው መጀመሪያ እነሱኑ ይሆናል። እንደነዚህ አይነት ጅሎችን አልፈውም ከተራ ዕቃነት ለይተው ስለማያዩዋቸው፤ የታዘዙትን ሁሉ ፈፃሚ አሽከር ሆነው የሚዘልቁበትን ሁኔታ ያመቻቹላቸዋል። ይህንን ሀቅ ከወያኔ አግአዚ ባሮችና ከሻዕቢያ ሎሌዎች ህይወት መገንዘብ ይቻላል። ብዙ ድንቁርና በጥቂት ብልጠት ሲፈታ ማየት ላገር ወዳዶች በሽታ በመሆኑ ባገራቸው አይደሰቱባትም። በዚህም ምክንያት ሀገር ለወዳጆቿ የሰላም ህይወትን ከመለገስ ትታገዳለች።

ሁልጊዜ ሲጀመር የግል ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ትግል መደምደሚያው በሌሎች ላይ ጭካኔና ወንጀል መፈፀም ነውና፤ ባለማወቅና ባለመረዳት መናጆ ሆኖ የሚሰለፈው ክፍል በብዙሃኑ ላይ የሚያደርሰው ጥቃትም በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። ስለዚህም ሀገር ለሚወዷት ሁሉ ምቹ እንዳትሆን ያግዳታል። በአንፃሩም ሀገራቸውን የሚወዱ ሁሉ፤ ስለነፃነትና ስለሰብአዊ ክብር የሚያስቡ ሁሉ፤ በውርደትና በልመና ተዘፍቆ በሀብት መክበርን የማይሹ ቀራጥ ዜጎች በመሆናቸው፤ ሀገርን ለገበያ በማቅረብ ሀብት ማካበትን፤ በሀገራቸው ህልውና ላይ ተደራድሮ ሶልዲ መልቀምን ስለሚጠየፉት፤ አስገድሎ መቀማትን ስለማይሹት፤ ህይወታቸው ሁሉ የጭንቅ ይሆንባቸዋል። ሞኟና ተላላዋ ሀገራችን ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ 'ከነሀለሿ ዓለም' የተለየች ትሆናለች ብለን ባናስብም በመጠኑም ቢሆን ከሞኝነቷ የምትወጣበትን ጊዜና ዘመን ለማቅረብ መጣር ግን ተገቢ ነው። በዚህም ላይ ግብግቡ ቀላል አይሆንምና፤ ጥቃቱና በደሉ፤ ሞቱና ድህነቱ ቢጎሻሽመን በሃገራችን ላይ ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም።

ከዚህ የትግል መድረክ ራቅ ብሎ የሚመለከት ወይም በማስመሰል ጊዜን ለመግፋት ብቻ ያለመ ወገን ካለ፤ ሁኔታውን በቅጡ ሳይገነዘብም ካገኘው ጋር የመደባለቅ ባህርይም ካጠቃው፤ ችግሩን ያባብሳል እንጂ! አያቀለውም። ሀገርም 'ሞኝና ተላላ' ተብላ እንድትዘልቅ ፈቀደ እንጂ! ሊያድናት፤ ሊያስለጥናት፤ አልተዘጋጀም። ለምሳሌ ወያኔን ብንመለከት የጎሳን ፍልስፍና ተከትለው የራሳቸውን ጎሳ ጥቅም ለማስከበር ብቻ ብለው በመወናበድ ለድርጅቱ ጋሪ ሆነው ለስልጣን ያበቁት አባላት በሙሉ ጥቅሙን አውቀውና ለይተው ያደረጉት ነው ብሎ ለማለት ያዳግታል። ምክንያቱም ኢትዮጵያን ማጥፋት ለትግራይ ብሄረሰብ ጥቅም ይሰጣል፤ የኢትዮጵያን ህዝብ እርስ በእርስ ማጋጨት፤ መግደልና ማስራብ፤ ማሰርና ማጋዝ፤ የትግራይን የበላይነት ይፈጥራል የሚለው የጥቂቶች ቅዠት ለሁሉም አስቀድሞ የታየ ራዕይ ነበር ማለት አያስደፍርምና።

ይልቅስ ከመነሾው በግል ቂምና በጎጠኝነት ስሜት ለተነሱ አጭበርባሪዎች ያለምንም በቂ ግንዛቤ አረንጓዴ መብራት በማሳየታቸው፤ ለእነ መለስ ዜናዊና አዜብ መስፍን፤ ለበረከት ስምኦን፤ ለአባይ ፀሐዬና ለአባዱላ ገመዳ፤ የሰርግ ዳንስ አስተናባሪ፤ ለሌሎችም ሀገርን ለማጥፋት መሰሪ ዕቅድ ላላቸው ሁሉ የዘረኝነት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ መሳሪያ ሆነው ወገናቸውን እንደጎዱ ነው መገንዘብ የሚቻለው።

ወያኔዎች ተዋጋንለት የሚሉት ድርጅት ኢትዮጵያን ለማጥፋት፤ የህዝብን መብት ለመርገጥ፤ የዲሞክራሲ መብትንም ለማፈን፤ አቅም ኖሮት ሲያዩ ከወንጀሉ ተጋሪ እንደሆኑ ከመቀበል ውጭ ሊያደርጉ የቻሉት ነገር አልተስተዋለም። በሀገር ውስጥ እንኳንስ ሌላውን እራሳቸውንም ነፃ ማድረግ አቅቷቸው ለውለታቸው የሚጣልላቸውን ዳረጎት እየለቀሙ ለመቀመጥ ተገደዋል። በውጭ ሀገርም ከጥቂት ሀገር ወዳዶች በስተቀር አብዛኞቹ የድል ቀን አክባሪዎች ናቸው። ድሉ በማ ላይ እንደሆነ ግን የሚያውቁት አይመስልም። ስህተቱ ከመነሻው ላይ ነበርና ሌላ ውጤት መጠበቅም አይቻል። ዛሬ እነሱን የሚተካ ሆዳም ከየአካባበው በመገኘቱ አስፈላጊነታቸውም እምብዛም ሆኗል። በዚህ አይነት መንገድ ሆዳምን በሆዳም እየተኩ ገዳዮች ሲበሉ ይኖራሉ ማለት ነው። ለደሃው ልጅና ለሀገር ወዳዱ ግን የተረፈው ያው ሞት ነው። በጠርነትም ሞት ይገጥመዋል። በሰላሙም ሞቱን እየሞተ ነው። ለስልጣን አምሮተኞች፤ ህዝብ ተጎታች ጋሪ ከሆነ ሀገርም "ሞኝ ነሽ ተላላ" ከመባል፤ የገደላትም ተንሰራፍቶ ከመብላት፤ የሚያስጥለው ነገር አይኖርም።

ይህንን በኛ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ዘግናኝ ሁኔታ ለመለወጥ የሚቻለው በቅድሚያ ከምን ላይ እንዳለንና ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ በቅጡ ስንረዳ ብቻ ነው። ዛሬ ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የዴሞክራሲ መብት የምናወራበት ጊዜ ሳይሆን ስለ ሀገር መኖርና አለመኖር የምንወስንበት ጊዜ ነው። ስለዚህም የሀገር ፍቅር ስሜትና ስለሀገር የሚደረግ ማንኛውም አይነት ትግል፤ መመራት የሚገባው ታሪክና ፍቅር ባላቸው አርበኞች እንጂ! ለቡርቦራ በሚያሴሩና ለዘላቂ ድል በማያበቁ አዋዥዎችና፤ ጨሌ ባንዳዎች አይደለም። ትግል በዚህ አይነቶቹ ሰዎች እጅ ውስጥ እንዲገባ መፍቀድም፤ ከውድቀት ሊያድነን አይችልም። ይህ አይነቱ ስህተት ሀገራችንን በተደጋጋሚ ችግር ላይ የጣላት ለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው የባንዳ ግለሰቦች ስልጣን ላይ መውጣት በቂ ምስክር ነው።

ስለዚህም የትግሉ ትኩረት ሀገርን ከእጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት ህዝብን ከባርነትና ከጭቆና ለማላቀቅ መሆን ይገባዋል። በፖለቲካ ልዩነት ላይ ተመስርቶ የኔ ይበልጥ! የኔ ይበልጥ! ማለቱ ምንም ፋይዳ የሚያመጣ ጉዳይ አይደለም። አንዱ ሌላውን ጥሎ የማለፍ ዓቅሙም ችሎታውም አይኖረውምና ፍትጊያው የሚፈጥረው የጋራ ውድቀትን ብቻ ነው። በእርግጥ ትግልን እንደሸቀጥ ለትርፍ የሚያቀርቡ አስመሳይ ታጋዮች ሀገር ወዳዱን የሚያዋዙበት ለመለያየት የሚችሉበት ቋንቋ አጥተው አያውቁም። ለጥቅም አቆብቁበው የሚጠባበቁ በመሆናቸውም ሁኔታውን እያጠኑ እራስን አመሳስሎ የማቅረብ ክህሎት አላቸው። ልክ እንደፋሽን ዛሬ እዚህ! ነገ እዚያ! እያሉ የሀገር ወዳዱን የትግል መንፈስ ለመለወጥ ይጥራሉ። ይህ አይነቱን ደባ በጊዜው መቅጨት ካልተቻለ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያችንን ከገባችበት አዘቅት ለማውጣት በቅድሚያ ትግሉን አቅጣጫና ዓላማ ማስያዝ ያስፈልጋል። ይህንንም ለመምራት በአንድ የፖለቲካ ድርጅት፤ በአንድ ብሔር፤ በአንድ ሃይማኖት፤ መደራጀት አያስፈልገውም።

ዛሬ ትግሉ የሀገር አድን ትግል ነው። ቀኟ ባሜሪካ፤ ግራዋ ባውሮፓ፤ መሃልዋ በእስያ ፈላጭ ቆራጭነት ስር የዋለች እናት ኢትዮጵያ፤ ላረብ ቱጃርና ለህንድ ባለሀብት ለአበባ መትከያ የተሸጠች ሀገርን፤ ለሆዳቸው ያስፈሰፋ ዜጎቿ በእድገትና በልማት በማሳበብ ላይ ተሰማርተው፤ ትርፍራፊ ሲለቅሙ ማየትን፤ ተወላጆቿ በሀገራቸው የስቃይ ህይወት እንዲገፉ የተደረገባትን ኢትዮጵያ ቆሞ ማየትን የመሰለ እርግማን የለም። ስለዚህም ለዚያች በጀግኖች ልጆቿ ተጋድሎ ታፍራና ተከብራ ለኖረች ሀገር፤ ተፈጥሮም፤ እንስሳውም፤ ወፉም፤ አራዊቱም፤ ሰውም፤ በአንድ ላይ ተነስቶ ይታገልላታል እንጂ በቀላሉ መላቀቅ አይኖርም። በፓርቲ ዲሞክራሲ ስም የትግሉን አቅጣጫ ለማሳት ወዳጅ መስለው ለሚቀርቡ አቸፍቻፊዎች ፊት ሊሰጣቸው ከቶ አይገባም። የዲሞክራሲ ትግል ማረፊያ ስፍራ ይፈልጋል። ሀገር በሚጠፋበት ሁኔታ ገዥን ለመምረጥ መጨቃጨቅ ብልህነት አይደለም። ጊዜው ሲፈቅድለት ሁሉንም አቅጣጫ ዳሰሶ

ታሪካቸውን አስተዋፅኦዋቸውን መርምሮና ቀራጥና ብልህ መሪዎችን ፈልፍሎ ለማውጣት ህዝብ ችግር የለበትም። የግንቦቱ ምርጫ ያሳየው ሀቅ ይህንን ነው። የወያኔን ካኒቴራ ለብሶ የተሰጠውን የገንዘብ ዳረጎት ተቀብሎ ነው በካርዱ መሪዎቹን የመረጠው። በዚህ ሀገርን የማዳን ጥያቄ ላይ አስመሳዮች ትግሉን ፈር ለማሳጣት መራወጣቸው ለዲሞክራሲም ሆነ ለሀገር ካላቸው ፍቅር ሳይሆን የሚያልሙትን እኔነት፤ በሌሎች ትከሻ ላይ ሰቅለው ለመዝናናት በመከጀላቸው ብቻ ነው። ስለዚህም ከታሪክ መማር የግድ ይላል። በነበላይ ዘለቀ አርበኝነት ተጋድሎ በነፃነት የቆየችው ሀገር፤ ጠላቶቿ ተሙነሽንሸውባታል። እነ በረከት ሀብተስላሴ የትምህርት ፀጋ አግኝተውባታል። እነ ኢሳይያስና እነለገሰ ዜናዊ ስማቸውን ቀይረውባታል። ዳግም መጭበርበር የለም። ዳግም ”ሞኝ ነሽ ተላላ” መባል የለም። ኢትዮጵያ የገደሏት ተዝናንተው የሚበሉባት፤ የሞቱላትም የሚዘነጉባት ሀገር መሆኗ ማብቃት አለበት።

የቅንጅት መሪዎች ለዚህ ሁሉ ችግር መፍቻ እንዳላቸው አሳይተዋል። ለእስር የዳረጋቸው አስተሳሰብም ይኸው ነው። የቅንጅት መሪዎች የነሱ በምርጫ ማሸነፍ ብቻውን የሀገር ዕድገትን ሰላምን ሊያስገኝ አለመቻሉን ጠንቅቀው ያውቃሉ። በማወቃቸውም ሁሉንም ያቀፈ የሀገሪቱን ህዝብ የፖለቲካ አመለካከት የሚያስተናግድ አመራር ለማስገኘት የሽግግር መንግስትን ለመመስረት ዝግጁነታቸውን ለህዝቡ ገልፀው ነበር። እምቢ ያለው ወያኔ ነው። እምቢተኞቹ፤ የወያኔን ፖሊሲ የሚያራምዱት ሆድ አደሮች ናቸው። ኢትዮጵያን የሚወድ ለሀገሩ የሚያስብ ዜጋ ካንድነት ከህብረት ውጭ ሰላም ይመጣል ብሎ አይገምትም። በቅንጅት እምነትና አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተው ሰላምና እርቅ ህዝብን ወደ አንድነትና ወደ ስምምነት ወደ እድገት እንደሚወስድ ጥርጥር የለውም። በአምባገነኖች እጅ ወድቀው ለስቃይ የበቁት የቅንጅት መሪዎች መንፈስም ይህ ነው።

መንፈሱን ገልብጠና ቀይሮ ቅንጅት ስልጣን ፈላጊ እንደነበር፤ መሪዎቹም ድርጅታቸውን ለስልጣን ለማብቃት ብቻ ሲሉ እንደታገሉ፤ አድርጎ መውሰድ ወያኔያዊ አስተሳሰብ ከመሆን አያልፍም። ቅንጅት መንፈስ ነው ያስባለው 'ሀቅ' ስለድርጅቱ ህልውና በማሰቡ ብቻ ሳይሆን የሀገርን ክብርና አንድነት ለመጠበቅ የሁሉንም ትብብር በቀና መንፈስ ተመልክቶ ዓላማውን ከፍ አርጎ ይዞ ለመጓዝ በመወሰኑ ነው። ይህም አስተሳሰብ ነው በዶር.ሀይሉ አርአያ ”ያገር ፍቅር ልክፍት” ግጥም ውስጥ የተንፀባረቀው። የቅንጅት መሪዎች የራሳቸውን ጥቅምና ክብር በሀገራቸው ክብር ለመለወጥ የተዘጋጁ እንጂ የድርጅትን ፍቅርና ጥቅም ለማምጠቅ የተነሱ አይደሉም።

ስለዚህም ሀገርን አስመልክቶ የሚደረጉ ትግሎች ሁሉ በጋራ የተቀናጁ መሆን አለባቸው። የቅንጅት መሪዎች የኢትዮጵያ ህዝብ መሪዎች እንዲሆኑ ህዝብ ድምፁን ሰጥቷቸዋል። ይህንን ድምፅ የማስከበር ሀላፊነት ያለበትን መራጭ ህዝብ መደገፍ ደግሞ የኛ ግዴታ ይሆናል። ይህ የሚሆነው በህብረት ነው። በተናጠል የሚደረግ ትግል ድልን ሲያስገኝ ታይቶ አይታወቅም። ኢትዮጵያን ለመታደግ አፍቃሪዋ በሙሉ እጅ ለእጅ ተያይዞ መጓዝ አለበት። የኢትዮጵያውያንን ፍቅርና የትግል መንፈስ ያድሳል ተብሎ በሚጠበቀው የ2ኛሺህ አመት በዓል አከባበር ላይም በውጭ ሀገር በሚኖሩት ዜጎች መሃል መንፀባረቅ የሚገባው ይኸው ነው። በጋራና በመተባበር ማዘጋጀት ይኖርብናል እንጂ! ለተናጠል የንግድ መናኸሪያ መድረክ ለማድረግና የወያኔን ገቢ ለመሻማት ታስቦ የሚዘጋጅ መሆን የለበትም። ይህን መሰሉን ህዝባዊ በዓል አስታኮ የግል ፖለቲካ ፕሮግራምን ለማስፈፀም የሚደረግ እንቅስቃሴ ካለም ካሁኑ ሊታረም ይገባል።

የ2ሺ ዓመት በዓልን በጋራ ለማክበር የሚያስችለው በየግል ማህበራትና ድርጅቶች ወይም የኤኮኖሚ ጥቅምን መሰረት ባደረገ ፎርሙ በግለሰቦች አቀናባሪነት በማዘጋጀት ሳይሆን ሁሉንም የሀገሪቱ ልጆች እንደ የስሜታቸውና ፍላጎታቸው እንደ ዐቅማቸውና ችሎታቸው የሚካፈሉበት ሰፊ

መሰረት ያለው መድረክ በመፍጠር ነው። የኢትዮጵያ 2ሺ ዓመት ክብረ በዓል ማንንም ያላገለለ መሆን ይገባዋል። አንዱን 'አራቁቶ ሌላውን አሸ-ሸምቶ' ሊያስኬድ የሚያስችል መድረክ እንዳይሆንም ጥንቃቄ ያሻል። የዳንስና የጭፈራ ብቻ ሳይሆን የፀሎትና ታሪክን የማሳያ ቀን መሆንም ይገባዋል። ስለዚህም በየአካባቢው የሚደረገውን ዝግጅት በጋራ የመቆጣጠር በጋራ የማዘጋጀት ሀላፊነት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ የሚወድቅ ይሆናል። ለዚህም የጋራ ኮሚቴ ፈጥሮ የዕድር፤ የዕቁብ፤ የሙያ የጓደኝነት ስብስቦችና ማህበራትን፤ ባሳተፈ መልኩ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው። ህዝቡ ተከፋፍሎ እንዲያከብር ከሚገፋፉ ሁኔታዎች መቆጠብ ያስፈልጋል። በገቢና በዝና ላይ ዓይንን ጥሎ በብቸኝነት ለመወጣት የሚያስብ ካለ ስህተት መሆኑን ካሁኑ መገንዘብ ይኖርበታል። ይህ በሰው አገር የምናከብረው የ2ኛው ሺ አመት በዓላችን ለመጭው ዘመን በሀገራችን ውስጥ ገብተን በፍቅርና በመተሳሰብ ተቃቅፈን የምንፈነድቅበትን ቀን የሚያመላክተን በመሆኑ ሁላችንም ተባብረንና ተጋግዘን የምናከበረው እንጂ! ግለሰቦችና ድርጅቶች በተናጠል የሚመሩት ጉዳይ አይደለም።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ቅን ህብረት እንደገና ታብባለች!

አመሰግናለሁ